# <u>አለን ባመፅ</u> (ቁጥር አምስት) (ከአጅሬው ዝብርቅርቅ ማህደር)

ካለፈው የቀጠለ

ግን መቃብሩ የፈካ ምልክት እንኳን የለውም። ሃውልትም አልተሰራለትም። ቤተሰቦቿ ሊያሰሩላት የገንዘብ አቅም ይኖራቸው አይኑራችው አላውቅም:: ግን ለኢሕአፓ ታጋይ ሃውልት ማን ነው የሚያቆመው"? ደረቁን የተኛችበትን አፈር ግን አሳይሃለሁ እኔ ምልክት አለኝ። በአመት አንድ ጊዜም ቢሆን ውሃ በኮዳ ቢጤ ነገር እየወሰድኩ በመጠኑ እንደጠበልም ቢሆን አፈስባታለሁ። ህያውነቷን ለመጠበቅ"። አልኩት ከዚህ በኋላ የሌሎቹን ሁለት አብረውን የታገሉ ወንድሞቻችን ታሪክ ማውራት አልፈለግሁም።
"እንግዲህ እንደሱ ከሆነ የሌሎቹን ታሪክ ስንገናኝ እናውራው። ሁሉንም ባንድ ጊዜ የሚከብድ ይመስለኛል። አይመስልህም? ሲል ጠየቀኝ
"ካልክ እኔም አሁን እርሱን ሳስብ ነበር"። ብየው ከአራት ቀናት በኋላ ጐላ ሚካኤል ተገናኝተን የፀሐይ ንጉሴን መቃብር . . . ተስማምተን ተለያየን።

**የፀሐይ ንጉሴ መቃብር**

እንደ ተለያየን እግሬም፣ ስሜቴም የመሩኝ በቀጥታ ወደ ፀሐይ ንጉሴ መቃብር ነበር። ለምን እንደሁ አላውቅም ለብዙ ጊዜ ያልተሰማኝ የእርጋታ ስሜት ውስጤ ውስጥ ሰላም ነገር ሲፈጥር ይሰማኛል። አረማመዴም ከወትሮው የተለይ ዝግታና ደረት መንፋት ነበረበት። ፀሐይ ንጉሴ መቃብር ላይ ስቀመጥ ሁል ጊዜ የሚመጣልኝ ደስ የሚለው ስሜቴን ዛሬ ከወዲሁ ተገናኘሁት። ከተኛችበት ስደርስ እንደምን ሰነበትሽ ፀሐይ አልኩና ከመቃብር ድንጋይ ላይ በሃሳብ እልም ጭልጥ አልኩ። ለሰአታት የሰላም እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደኝ። ስነቃ ካሁን ቀደም አጎቴ ነመራን በተኛሁበት አናግሬ ስነሳ የተሰማኝን ያህል ጉልበት ተሰማኝ። ፀሐይ ንጉሴን እንደገና እንዴ ሰነበትሽ ሃውልታችን፤ ምነው ዘንድሮ ምን አግኝቶ ለሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ መጣ ሳትይ እንዳልቀረሽ ይገባኛል። ሰሞኑን እንግዳ ይዥብሽ ልመጣ ስለሆን እርሱን ልነግረሽ ነው የመጣሁት። አምስት ሆነን ባንድ ህዋስ ውስጥ ስንታገል ከነበርነው መካከል ከሊፋና ክብረት ጋር አሁን ያላችሁበት ሳትገናኙ አትቀሩም። ተገትረን በህይወት የቀረነው እኔና የትግል መሪያችን ሆኖ ሲያታግለን የነበረው በኋላ ሊገደል ሲፈለግ የጠፋና ካልገደሉት ወደ በረሃ ወጥቶ ይሆናል ያልነው ሰው ነው። ከአሜሪካን አገር መጥቶ መሃል መርካቶ በአጋጣሚ ተገናኘን። እነሆ እንግዲህ ያንቺን መስዋዕት መሆን ነግሬው ሊያይሽ ከፈለገ እንደማመጣው ቃል ገብቸለት ከአራት ቀናት በኋላ ሊመጣ ቀጠሮ ይዘናል። አልኳትና አርፌ ቁጭ ብየ ምስኗን ከህሊናዬ አውጥቼ በህዋው ላይ ሰቅዬ አስተውላት ጀመር። ፀሐይ ከእኔ ሌላ እየመጣ የሚጐበኝሽ ሰው እንዳለ አላውቅም። ዘንድሮ ግን እነሆ ሁለት ልንሆን ነው (በየአመቱ ኢሕአፓ የተወለደበትን ጊዜ እያስታወስኩ በዚህ ጊዜ ነው ወደ ፀሐይ እየሄድኩ አመቱን የማከብረው)። የጊዜ ነገር አይገርምም። ከሃያ ሰምንት አመታት ታጋይ ሁሉ በየቦታው በተዘራበት አገር ከእኔ ጋር ባረፍሽበት መሬት ላይ የሚቆም ሰው ማግኘቴ። ቅድም እንዳልኩሽ አሜሪካ ነዋሪ የሆነው የትግል መሪያችን የእናንተን መስዋዕትነት መክፈል ስነግረው ምርር ብሎ አለቀሰ። ዘንድሮ ያለውን አቋም ባላውቅም ያው እንዳልኩሽ ከአራት ቀናት በኋላ መጥቶ ያይሻል። ያናግርሽ ይፈልግ ከሆነ ለብቻችሁ እተዋችኋለሁ። መቼም ማለት የሚፈልገው ነገር ሳይኖር እንደማይቀር አምናለሁ። ያ ሁሉ ስቃይ ሲወርድብሽ የእርሱንም፣ የእኔንም፣ የሌሎችንም ስም ካፍሽ ሳታወጭ እንደተሰዋሽ ነግሬዋለሁ። መቼም ፀሐይ አንድ ሰው ወደ አገሩ ሲመጣ ወደ አገሩ ተመለሰ እንጅ ለጉብኝት መጣ አይባልም። ይህ ወደ አገሩ የተመለሰ የትግል መሪያችን የነበረ ሰው አገሩ መመለሱ ለጉብኝት ወይም ለመዝናናት አይመስለኝም። ምንም የተመቸው ቢመስልም አገሩ ሁሉ ነገሩ ይመስለኛል። እርሱም ቢሆን የከፈለው መስዋዕትነት ቀላል

አይደለም። በቀደም ስናወራ ምን አለኝ መሰለሽ "እስኪ ላለፈ ጊዜ ስንል አምስታችንም እንገናኝ" መስዋዕትነታሁን ስነግረው ስለእናንተ የማውቀውን እንድነግረው ጠየቀኝ። ታሪካችሁ አገር የሚያኮራ ነው መነገር አለበት፣ ለትውልድ መተላለፍ አለበት አለኝ። መፅሐፍም ይፃፍበት (ዕፎ ከከበረም ምን አለበት ደማችን ነው) በቃሉም ለልጆቹ ለባልንጀሮቹ ይናገረው ታሪካችሁን መንገር ጀምሬለሁ። በይ እንግዲህ ከአራት ቀናት በኋላ እመለሳለሁ ብያት በየአመቱ እንደማደርገው የእጄን መዳፍ ሳም አድርጌ የተኛችበትን መሬት ነካሁና በዝግታ እርምጃ ቤተክርስቲያኑን ተሳልሜ ከባቢውን ለቀቅሁ።

አራቱ ቀናቶች ክንፋቸውን አውጥተው በረሩ። ከቀጠሮው ሰአት ቀደም ብየ ከባቢውን በሩቅ ስቃኝ (አለ አይደለም ጥንቃቄ ወታደር ሳይሆኑ ደርሶ ወታደር መሆን) ቀይቼ ችግር አለመኖሩን ካጠናሁ በኋላ የትግል መሪየ የሆነውን ሰው አየሁት። ከኋላው "ደርሼ አገሬውን አትመስልም የሌላ አገር ሰው እንደሆንክ ታስታውቃለህ" ብየ ለሰላምታ እጄን ዘረጋሁ። እጄን አፈፍ አርጎ ጉትቶ በእቅፉ ሰላም ካለኝ በኋላ
"አገሬ ነው እኔም የአገር ሰው ነኝ ጥቂት ብሰነብት አንተኑ መስዬ ነው የምገኝ"። አለና "ግን አሁን ምኔ ነው የተለየው" አለና እንደልማዱ ትቀልድብኛለህ አይደል ሲል
"እንዴት ነህ? ወደ አገርህ የመጣህበት ተሞላልህ ስል ጠየቅሁት" ለምን እንኳን እንደመጣ ሳላውቅ
"ደህና ነኝ የመጣሁት ለዕረፍትና አገሬንና ቤተሰቦቼን ላይ ነው እንጂ ሌላ ጉዳይ እንኳን የለኝም"። ብሎ እርምጃችንን ወደቤተክርስቲያኑ ጀመርን።
"በቀደም ካንተ ጋር ስንለያይ መንገዴን ወደዚህ አቅንቼ ለፀሐይ ስለድንገተኛ ግንኙነታችንና ዛሬ ወደዚህ አብረን እንደምንመጣ ስለነገርኮት በጉጉት ትጠብቀናለች" ስለው እንደመደንገጥም እንደመገረምም አድርጎት ቆም ብሎ አስተዋለኝ።
ፀሐይ ንጉሴ መቃብር ስንደርስ ቆም አልኩና መዳፌን ሳም አድርጌ የተኛችበትን መሬት ነካሁና "ፀሐይ ይኸውልሽ በቀደም በነገርኩሽ መሰረት የትግል መሪያችንን የነበረውን ሰው ይዤልሽ አብረን መጥተናል"። "እስኪ እይው እንዴት እንዳማረበት ከነኝህ ሁሉ አመቶች በኋላ አንድ ፀጉር የነቀለ አይመስልም። አላማረበትም?"። ስላት የያዘውን የሚያምር አበባ ካረፈችበት መሬት ላይ በጥንቃቄ ዘርጋ አድርጎ አስቀመጠና ልክ እኔ እንዳደረግሁት ጣቶቹን ሳም አድርጐ የተኛችበትን መሬት ነካ አደረገና ቀና አለ። የዛሬ አቋሙን አልወቅ እንጂ ለፍቅሩ በጣም አከበርኩት። አብሬው ከእርሱ ጋር በኢሕአፓነት የታገልኩባቸውን ዘመኖችም የባሰ ወደድኳቸው። አንጀቴ ውስጥ ምስቅልቅል ያለ ስሜት ሲስምጥ ይሰማኛል። እንባወች በአይኔ ሞሉ። ፀሐይ መቃብር ላይ መጥቼ አልቅሼ አላውቅም ይህ የመጀመሪያየ መሆኑ ነው።
"አመሰግናለሁ ለአክብሮትህ በጣም አመሰግናለሁ" ከማለት ሌላ ስሜቴን ልገልፅ ተቸገርኩ። "ፀሐይ እነሆ ሁለት ሆነን መጣን። ምንም እንኳን አድናቂሽ፣ አክባሪሽና የሚወድሽ ቁጥር ስፍር ባይኖረውም ለዛሬ እነሆ ሁለት ሆነን መጣን። እስኪ ሁለታችሁን ለጥቂት ጊዜ አብራችሁ ልተዋችሁ"። ብየ የእርሱን መልስ ሳልጠብቅ ዘወር አልኩ። ከፀሐይ ራስጌ የተቀመጠው ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ ክርኖቹን ጉልበቶቹ ላይ አሳርፎ በመዳፎቹ ጉንጮቹን ተደግፎ እንዳቀረቀረ ብዙ ቆየ። ከሩቅ ሳስተውለው አልፎ አልፎ የሚያወራት መሰለኝና የበለጠ ደስ አለኝ። ተመልሼ በል እንግዲህ ከተጣገባችሁ እንሂድ ጊዜ ካገኘህ ተመልሰህ ታያታለህ" ስለው በዝግታ ተነሳ። ከያዝኩት ውሃ እንደልማዴ እነሆልሽ ጠበሉ በትግል መሞት ሕይወት የተዘመረበት ብየ ከአፈሯ ላይ አርከፈከፍኩና እንደጀመርነው መቃብሯን ስመን ቤተክርስቲያኑንም እንሳለም ብየው ተሳልመንና ከባቢውን በዘግታና በዝምታ ለቀቀን። ስለፀሀይ ንጉሴ ከዚህ በኋላ ምንም አላወራንም ነገር ግን ወደ ፀሀይ ንጉሴ መቃብር እየሄድኩ እንደምጎበኛት የሚያውቅ ከርሱ ሌላ ማንም እንደሌለ እንደነገርኩት አስታውሳለሁ።

የቤተክርስቲያኑን ከባቢ ለቀን ዘወር ካልን በኋላ አንዲት ሰዋራ ስፍራ አረፍ አልን። ስለሌሎቹም ወንድሞቻችን መስዕዋትነት ላወራው ቃል ብገባለትም ዛሬውኑ ባይሆን ፈልጌ ነበር። ሆኖም መሄጃየም እየቀረብ ነው ካሁን በኋላ ብዙ መገናኘት አንችል ይሆናል ስላለኝ የክብረትን መስዋዕትነትና የተፈጠረውን በዚሁ ቀን አወራሁት።

ክብረት ሞላ

ስለክብረት መናገር ስጀምር ልክ ስለፀሐይ ንጉሴ መናገር እንደጀመርኩት አድርጌ ቅደም ተከትል እንዳላወጣሁለት በአእምሮየ የመጣውንና የማስታውሰውን ብቻ እንደማወራው በተቻለ መጠን የገዳይ የአጋዳይ ስሞቹን ሳልጠቅስ የራሴንም ስሜት ለራሴ አስቀርቼ እንደምተርክለት ነግሬው ግን ታሪኩ ጠንከር ያለ ሂደት እንደነበረው አስረድቸው ነበር ታሪኩን የተረኩለት።

የክብረት አገዳደል ፍጥነት የሞላው ነበር። ታውቅ አታውቅ እንደሆን አላውቅም እንጂ ክብረት የወታደር ልጅ ነው (ነበር አልልም አሁንም ህያው ነውና)። አባቱ ኮርያ ይሁን ኮንጎ ወይም ሁለቱም ቦታ የዘመቱ አምሳ አለቃ ናቸው። ልጃቸው እንደጠፋ ያወቁት በተያዘ ማግስት ነበር። ከሰፈር ባልንጀሮቻቸውና ቤተዘመዶቻቸው ጋር በመሆን ወደሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ቢሄዱ የለም ተባሉ። አብረዋቸው ለሄዱት ሰፈረተኞች አንዱ በሰፋራቸው ኖሪ የሆነ ፖሊስ ማታ ጣቢያ አምጥተውት ሌሊቱን እንደወሰዱት በመጠቆሙ ከጊዜው ጋር በተያያዘ የሰፈር ሰዎች ተሸቀዳድመው ወደምኒሊክ ሆስፒታል የሬሳ ቤት ሄዱ። ሬሳ ቤት የሚገባ ደፋር ቶሎ የክብረት ወላጆችና ቤተዘመዶች ሳይመጡ ተባለና አንዱን ወጣት አንተ ግባ አንተ ግባ ተብሎ ከሬሳወች መካከል አንገቱን አርደውት ሬሳውን አይቶ እየተንቀጠቀጠ ወጥቶ ለሰፈረተኞቹ ነገረ (ይህ ወጣት ከተገደሉ ወጣቶች መካከል የክብረትን መኖርና አለመኖር ለመለየት ሲሞክር በተመለከተው የተነሳ ለብዙ ጊዜ የአእምሮ ታማሚ ሆኖ ነበር በኋላም ራሱን አንቆ ገደለ)። ቤተሰቦቹን የለም ብሎ ወደቤታቸው የሚመልስ መላና መልዕክተኛ አዘጋጅተው ወደሰፋራቸው ተመልሰው ድንኳን በፍጥነት አስጣሉ። ድንኳኑ በለቀስተኛው ሞልቶ ዋይ ዋይታው ቀጥሎ ሬሳውን ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል እንዲያመጡ ስራ የተሰጣቸው ሰዎች በወቅቱ ለተገደል "አናርኪስት" የሚከፈለውን ገንዘብ (ለጥይት መሆኑ ነው፤ ነገር ግን ክብረት የተገደለው በጥይት ሳይሆን አንገቱን ቆርጠውት ነው) ከፍለው ሬሳውን አምጥተው ከቤት አረፈ። አመሻሽ ላይ ከመኝታ ቤታቸው ሳይወጡ የቀሩት አባቱ አምሳ አለቃ ሞላ ይሁኔ ወደ ድንኳኑ መጥተው መንቀራጠጥ ጀመሩ።

ይቀጥላል

አጅሬው ዘብሔረ መርካቶ (ከመርካቶ)